# ዘገባ ከሰማይ ቤት

## ክፍል-አንድ

*በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)*

ነፍስ እባላለሁ። የሰው ነፍስ! ብዙ ቦታዎች ኖሪያለሁ፤ አሁን ግን በሰማይ ቤት እገኛለሁ። እድሜዬ በቁጥር አይገለጽም። እውነቴን ነው! እንዲሁ እድሜአቸው ከአስር አመት በታች እንደሆኑት ልጆች ቶሎ ለማደግ በመመኘት ወይም ደግሞ እድሜ በክርኑ ጎሽም እንዳደረጋቸው ሰዎች ወጣት ለመባል በመከጀል ሳይሆን እድሜዬን መቁጠር ስለሚያስቸግር ነው። ጾታዬን በተመለከተ እንደ ወንድ የሚያዩኝ ባይጠፉም ብዙዎች በሴት ይመስሉኛል። “ቀጭን ካልሆነች በሞት ጊዜ እንዴት ሺው ብላ ከስጋ ታመልጣለች?” በሚል ግምት ይመስለኛል ሰዎች ከክርም የቀጠንኩ ቀጫጫ አድርገው ይገምቱኛል። አንዳድ መደመርና ማባዛት ሳይሆን መቀነስና ክፍልፋይ የሚወዱ ያልተባርኩ ፍጡራን ደግሞ የዚህኛው ቋንቋ ተናጋሪ ነፍስ፣ የዚያኛው ነገድ ነፍስ፣ የዚህኛው መንደር ነፍስ፣ ምንትስ- ምንትስ  እያሉ ብዙ መልክ ሲሰጡኝ ይሻሉ። እኔን ግን ይህ ሁሉ አቴቴ የማይገልጠኝ በምድር በስጋ ተሸፍኘ በሰማይ ደግሞ ከስጋ ተለይቼ የምኖር መንፈስ ነኝ። የተወሰነ  ጾታ፣ እድሜ፣ ወርድ፣ ቋንቋ፣ የዘር ግንድ፣ ክልል ጎጥና ሌላም መስፈሪያ የለኝም። ዝምብዬ ነፍስ ነኝ! ወዲያውም  በጭንቅ ካልተወጠራችሁ በስተቀር አታስታውሱኝም እንጅ በእያንዳንዳችሁ ገላ ውስጥም እገኛለሁ ። ልብ ብላችሁት ከሆነ አንዳንድ ሰዎች የደስታ መግለጫ፣ የጨዋታ ማሳመሪያ፣ የእንጀራ መበያ፣ የጽዋ መጨበጫ፣ የሹመት መረማመጃ፣ የንብረት ማካበቻ፣ የክህነት መካኛ ሁሉ ሲያደርጉኝ ይውላሉ።

አዎ እንደ ቲፍኒ (እናት ያዋጡት ስም ትርፍነሽ) የፈለጉትንና የወደዱትን ልብስ፣ ጌጣጌጥ፣ የትዳር ጓደኛና ሌላም ሌላም ነገር ሲያገኙ “እምጿ” ብለው ይስሙና “ነፍስ ነው!” ብለው ደስታቸውን ይገልጹብኛል። እንደ ወይዘሮ ታንቾወዲያ ያሉት ወይዛዝርት ደግሞ “ነፍስ ውጭ ነፍስ ግቢ” የሚለውን ተረት እየተረኩ የጭንቀት መግለጫ ያደርጉኛል። እንደ ቄስ ቀረበከንቱ ያሉትም “የሞቱትን ነፍስ ይማር” እያሉ መስቀላቸውን ባራቱ አቅጣጫ ቀስረው ድግስ እየባረኩ በሳልስት፣ በሰባት፣ በሰላሳ፣ በአርባ፣ በሙት-አመት የጥዋ መጨበጫ ያደርጉኛል። እንደነ አቡነ ግፍ-ምግባሩ፣ ጳጳስ ሆድ-አምላኩና መነኩሴ ድሮቀረ አይነቶችም “መንኩሰ ሞተ” የሚባለውን አባባል ረስተው እነ ወይዘሮ ጠቢያው እጨት እየሸጡና ጠላ እየጠመቁ ለነቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ሚካኤል ወዘተ ባስገቡት ስለት የጠበደለ ገላ በካባ ሸፍነውና አሸክመው ከተማ ለከተማ ይርመሰመሱብኛል። ለቀባሪው ማርዳት አይሁንብኝ እንጅ እነ ስልጣን-ነፍሱም የለበስኩትን ስጋ በጥይት በርቅሰው ጥለው ወይም በርሃብና በበሽታ ሞሽልቀው ወንበር ላይ ጉብ ይሉብኛል። አዎ በነሱ አካል እንደሌለሁ ሁሉ አሳደው፣ እሰረው፣ ንብረቱን ግረፈው፣ በመርዝ አፍነው፣ በጣጣቴ ተኩሰው፣ እንደ ዶሮ ስቀለው፣ ወዘተ እያሉ እኔ ነፍስ የለበስኩትን ስጋ ያሰቃዩብኛል።

“በክርስትና እምነት አምላክ አንድም ሶስትም ነው” እንደሚባለው እኔንም አንዳንዶች አንድ፣ ሌሎች ደግሞ ሁለት፣ ሶስትም፣ ብዙም ያደርጉኛል። “ነፍስ አንድ ናት!’ የሚሉት በተፈጥሮዬ ይመስለኛል። እኔ የማልሸተት፣ የማልሰማ፣ የማልታይና የማልዳሰስ ስለሆንኩ አንድ መስዬ በልቡናቸው እታያቸዋለሁ። ሁለት ናት ብለው የሚራቀቁት ደግሞ በሌላኛው አለም በሚኖረኝ ስፍራ ነው ብዬ አምናለሁ። ከማይቀዘቅዝ ወይም ከማይወብቅ፤ ርሃብ፣ በሽታና ቸነፈር ከሌለባት ገነት ውስጥ የምትኖር የተቀደሰች ነፍስና እጅግ ከጋለ ብረት ምጣድ ላይ እንዳስቀመጡት ስብ ወይም ዘይት ዘላለም እየተንጫረረች ሲኦል ውስጥ  የምትኖር ነፍስ! “ነፍስ ሶስት አይነት” የሚሉት ደግሞ በምድር በሚኖረኝ ስፍራ ነው ብዬ አምናለሁ። አብራራ ካላችሁኝም አንደኛ ለሰብአዊ መብት መስፈን ኑሮዋን በመሰዋቷ ወይም ለሰው ልጅ ወይም ለሌሎች ፍጡራን የሚበጁ ጥበቦችን ለመፍጠር ጊዜዋን በመለገሷ በትውልድ ስትመሰገን የምትኖር ቅዱስ ነፍስ፤ ሁለተኛ ደግሞ በሌሎች ሰዎች ወይም በአጠቃላይ በተፈጥሮ ላይ በፈጸመችው አሰቃቂ ግፍና መከራ በልጅ አዋቂው ከአለም ፍጻሜ በኋላም ስትረገም የምትኖር እርጉም ነፍስ፤ ሶስተኛ እንደዚሁ ከሁለቱም ሳትሆን እንዲሁ እንደ ጉንዳን ወይም እንደ አሳማ ስትበላ ኖራ በምድር ላይ ምንም አሻራ ሳትተው የምትጠፋ ትንኝ ነፍስ! “ነፍስ ከሶስትም በላይ ናት!” ብለው የሚከራከሩበትን ጉዳይ እንደገና ስንገናኝ አወጋችኋለሁ። እስከዚያው ግን ይህ ሆድ፣ ገንዘብ፣ ስልጣንና ሌላም ሌላም መቅቡጥ የሚያማልለው ገላችሁ ደፍቆ ወይም እያቀበዘበዘ የያዛት ነፍሳችሁ ከየትኛው እንደምትመደብ እያሰላሰላችሁ እንድትቆዩኝ በትህትና እለምናለሁ! አመሰግናለሁ።

ነፍስ ነኝ! ከሰማይ ቤት።

*ጥር ሁለት ሺ ሁለት ዓ.ም.*